የሰ/መ/ቁ. 234991

ሚያዝያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነው

**አመልካች፡-** የአ.ብ.ክ.መ ቴክኒክና ሙያ ቢሮ

**ተጠዎች፡-** 1ኛ.ብርሃኑ ነጋ ህንፃ ስራ ተቋራጭ

2ኛ.ናይል ኢንሹራንስ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የግንባታ ውልን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው ክስ መጋቢት 06 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገ ውል 1ኛ ተጠሪ በብር 3,119,240.10 ዋጋ በደቡብ ወሎ ዞን ከላላ ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጅ የጀነራል መካኒክ ግንባታ በ120 ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ ግዴታ ገብቶ 2ኛ ተጠሪን በዋስትና በማቅረብ ቅድመ ክፍያ ብር 742,997.40 ከወሰደ በኋላ ስራውን ለማጠናቀቅ ባለመቻሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ውሉ መቋረጡን ጠቅሶ 1ኛ ተጠሪ ግንባታውን በማዘግየቱ ቅጣት ብር 312,924.00 እንዲከፍል፤ ከወሰደው ቅድመ ክፍያ ያልመለሰውን ብር 513,727.10 እንዲሁም የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ብር 284,854.40 ከወለድ ጋር ዋስትና ከሰጠዉ 2ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉት ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጠው መልስ ስራዉ የተጓተተው በአመልካች ጥፋት በመሆኑ የመልካም ስራ አፈፃፀም እና የመቀጮን ገንዘብን ልከፍል አይገባም፤ አመልካች ውሉን ያቋረጠ በመሆኑም የመዘግየት ቅጣት ልከፍል አይገባም፤ የደረሰ ጉዳት በሌለበት መልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ቅድመ ክፍያውን አስመልክቶ በውሉ ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ያላቀረበ በመሆኑ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በውሉ አፈፃፀም ላይ ጉድለት የፈፀመ ስለመሆኑ በፁሁፍ ሊያሳዉቀዉ እንደሚገባ በዉሉ የተመለከተዉን ግዴታ አመልካች አለመወጣቱን፣ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ የሚጠየቀው ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ በመሆኑ አመልካች ቀሪ ስራውን ያሰራው ከውሉ ገንዘብ ባነሰ ገንዘብ ስለሆነ ተጨማሪ ወጭ እና የደረሰ ኪሳራ ስለሌለ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ ውሉ የተቋረጠው በጥፋቱ ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ ከወሰደው ቅድመ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ ያልመለሰውን ገንዘብ ብር 513,727.10 ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል። የግንባታ ዉሉ የተቋረጠ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የመዘግየት ቅጣት ክፍያ የሚጠየቅበት የህግ አግባብ የለም። አመልካች በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ውሉ እና በህጉ በተጣለበት ግዴታ መሠረት 1ኛ ተጠሪ በውሉ አፈፃፀም ላይ ጉድለት የፈፀመ መሆኑን በፅሁፍ ያላሳወቀዉ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ ያልመለሰውን ቀሪ ገንዘብ 2ኛ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም። አመልካች ቀሪ ስራውን ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ በልዩነት የደረሰበት ተጨማሪ ወጪ እና ኪሳራ በሌለበት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም እነዚህ በስር ፍ/ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን ለማስለወጥ ነው።

አመልካች መስከረም 23 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ዋና አላማው ውል ተቀባይ በውሉ መሰረት ግንባታ ስራውን መስራት ካልቻለ ይህንኑ ገንዘብ ጉዳት ደረሰም አልደረሰም የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት በአ.ብ.ክ.መ የመንግስት ግዥ መመሪያ ቁጥር 1/2003 አንቀፅ 14.20(4) እና በፍትሐብሔር ህጉ ቁጥር 1989 እና ተከታዮቹ ከተመላከተው ድንጋጌ ዉጪ ዉሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ ተጠሪዎች የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘቡን የመክፈል ሃላፊነት የለባቸውም መባሉ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የቅድመ ክፍያ ገንዘቡን መመለስ እየተገባው በውሉ የተቀመጠውን የማሳወቅ ግዴታዉን አመልካች ተወጥቶ እያለ እንዳልተወጣ በማድረግ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በአመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት ስለሌለ ተጠሪ የመልካም ስራ ዋስትና ሊከፍል አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነበት አግባብ ከክልሉ የመንግስት ግዥ መመሪያ ቁጥር 1/2003 መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል። በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ጥር 05 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በቀን መጋቢት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል። አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ዉል መሠረት ተጠሪ ለመልካም ስራ አፈፃፀም ብር 284,854.40 ለአመልካች ለመክፈል ግዴታ ገብቶ ለአፈፃፀሙም ዋስትና ከ2ኛ ተጠሪ ስለማቅረቡ አላከራከረም። ከላይ እንደተገለጸዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የአማራ

ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን አስመልክቶ አመልካች ያቀረበዉን ዳኘነት ዉድቅ ያደረገዉ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበረዉን ዉል አቋርጦ ለሌላ ስራ ተቋራጭ የሰጠዉ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ዉል ላይ ከተመለከተዉ ዋጋ ባነሰ ዋጋ በመሆኑ ዉሉ በመቋረጡ ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰ ኪሳራ የለም በማለት ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከመንግስት መስሪያ ቤት ጋር ከሚደረግ ግዥ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸዉ ህጎች ከተዘረጉት የዉል አመሠራረት ሂደቶች ዉስጥ አንዱ ሻጩ የዉል ማስከበሪያ እንዲያቀርብ የሚገደድበት ሥርዓት ነዉ፡፡ የፌዴራል ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 47 አቅራቢዉ በዉሉ መሠረት ባለመፈጸሙ በመንግስት መስሪያ ቤቱ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት ማካካሻ የሚዉል የዉል ማስከበሪያ ለባለበጀቱ መስሪያ ቤት መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣዉ የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 16፡25 (2) በአቅራቢዉ ያልተሟላዉ የዉል ግዴታ በመስሪያ ቤቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢዉ ቸልተኝነት ምክንያት የተፈጸመ አለመሆኑ በመስሪያ ቤቱ የግዥ አጽዳቂ አካል ሲታመንበት የዉል ማስከበሪያዉ ለአቅራቢዉ ሊመለስለት እንደሚችል ያሳያል፡፡ የክልሉ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 አንቀጽ 34 አቅራቢዉ በዉሉ መሠረት ባለመፈጸሙ ምክንያት በግዥ ፈፃሚ አካሉ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት ማካካሻ የሚዉል የዉል ማስከበሪያ ለግዥ ፈፃሚ አካሉ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ስራ ላይ የዋለዉ የክልሉ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2003 በትርጉም ክፍሉ የዉል ማስከበሪያ ማለት አቅራቢዉ በዉሉ መሠረት ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚደርሰዉን ጉዳት ለማካካስ እንዲቻል በአቅራቢዉ ስም ለዉል ሰጪ ግዥ ፈፃሚ አካል የሚሰጥ ዋስትና ስለመሆኑ ይደነግጋል (አንቀጽ 3/2/ ይመለከቷል) ፡፡

ከዚህ ሁሉ በተለይም *"ለሚደርሰዉ ጉዳት"* በሚል ከተገለጸዉ ሐረግ መገንዘብ የሚቻለዉ ከመንግስት መስሪያ ቤት ጋር የሚደረግ ግዥን አስመልክቶ የሚሰጥ የዉል ማስከበሪያ ዋስትና ዓላማ አቅራቢዉ በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ምክንያት በገዥዉ መስሪያ ቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ማካካሻ እንዲሆን መሆኑን ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በዉሉ የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ የግንባታ ስራዉ ለሌላ አካል የተሰጠ ቢሆንም ይህ በመሆኑ ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት አለመኖሩ በስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን ተቀብሎታል፡፡ አመልካችም በዉሉ አለመፈጸም ምክንያት የደረሰበት ጉዳት አለመኖሩን ተቀብሎ ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ኃላፊነት አለባቸዉ በማለት አጥብቆ የሚከራከረዉ በአመልካች ላይ ጉዳት ባይደርስም በመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትናዉ ላይ የተመለከተዉ ሊከፈል እንደሚገባ በክልሉ የግዥ መመሪያ ቁጥር 1/2003 ላይ ተመልክቷል በማለት ነዉ፡፡ ይሁንና ስለ የዉል ማስከበሪያ ዉጤት የሚደነግግገዉ የመመሪያዉ አንቀጽ 14.20 ጉዳት ያልደረሰ ቢሆንም ገዥዉ መስሪያ ቤት የያዘዉን የዉል ማስከበሪያ ገንዘብ እንዲወርስ ወይም ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢዉ ተዋዋይ ለዉል ማስከበሪያ በዉሉ የተመለከተዉን ገንዘብ ለመመለስ እንደሚገደድ በግልጽ አያሳይም (አንቀጽ 14.20 ንዑስ አንቀጽ 2-5 ይመለከቷል)፡፡

በሌላም በኩል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ

ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በዉሉ አግባብ ባለመፈጸሙ ምክንያት አመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት ባይኖርም ዉሉን ባለመፈጸሙ ምክንያት ብቻ በዉሉ የተመለከተዉን የመልካም አፈፃፀም ዋስትና ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት አመልካች የሚያቀርበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ በጸናዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 41864 ላይ መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 226388 ላይ ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ